# ወርሓዊ ዜና ሚቲዎሮሎጂ

## Monthly Met. News



የለውጥ ትግበራ ሥልጠናዊ ዐውደ-ጥናቱ ሲካሄድ







ቅፅ 4 ቁጥር 5 የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ኅዳር 2010 ዓ.ም

# በተቋማት የሥራ አፈጻጸም ላይ ተጨባጭ ለውጥ በማምጣት የዜጎችን ርካታ ለማረጋገጥ የሚያስችል በሪፎርምና መልካም አስተዳደር ትግበራ ዙሪያ ያተኮረ ሥልጠና ለመላው የኤጀንሲው ሠራተኞች ተሰጠ

### *"የመልካም አስተዳደር ማነቆዎችን እየፈታን የሕዝብ አገልጋይና ደጀን የሆነ ፐብሊክ ሰርቪስ መገንባት የሞት የሽረት ጉዳይ ነው" የውይይቱ መሪ-ቃል*

ሥልጠናዊ ውይይቱ የተካሄደው ከኅዳር 11-16 ቀን 2010 ዓ.ም ሲሆን ሁሉም ሠራተኞችና ከክልል ሚቲዎሮሎጂ ማዕከላት የመጡ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች ባጠቃላይም ከ300 በላይ ተሳታፊዎች በተገኙበት ቦሌ በሚገኘው በኤጀንሲው ዋና መሥሪያ-ቤት የመሰብሰቢያ አዳራሽ መሆኑ ታውቋል።

ይኸው ለአምስት ቀናት የተያዘው መርሐ ግብር የውጤት ተኮር/BSC ማሠልጠኛና አተገባር ሰነድ፣ የመልካም አስተዳደር ማሠልጠኛና አተገባበር ሰነድ፣ የፐብሊክ ሰርቪስ የሥነ-ምግባር ኮድ፣ የዜጎች ቻርተር ማሠልጠኛ ሰነድ፣ የለውጥ መሣርያዎች ምንነትና ትስስር፣ የስብሰባ አመራር መመሪያ፣ የለውጥ ሠራዊት ግንባታ ሰነድ በሚሉ በሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በተሰናዱ ሰነዶች ላይ ገለጻና ሰፊ ውይይት ተካሂዷል።

በሥልጠናው ወቅት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ እንደተናገሩት የሥልጠናው ዓላማ ሲቪል ሰርቫንቱ ለኅብረተሰቡ ስለሚሰጠው አገልግሎት ዘመኑ የሚጠይቀውን ደረጃና መስፈርት ያሟላ እንዲሆንና በአገልግሎት አሰጣጡም ሆነ በውስጥ አደረጃጀት ላይ ያሉትን ማነቆዎች መፍታት በሚያስችል መልኩ የታቀደ መሆኑን ገልጸዋል። ዋና ዳይሬክተሩ አክለውም፣ ሥልጠናው በዕቅድ የተያዘው የአቅም ግንባታ አካል መሆኑን አስታውቀው ሲቪል ሰርቪሱ የኪራይ ሰብሳቢነት ምሽግ የሆኑትን ማነቆዎች ለማስወገድ ራሱን በለውጥ መሣርያዎች ማስታጠቅ እንደሚያስችለው፣ አሳስበው፣ ይኸም ለፈጣንና ቀጣይ ዕድገታችን ወሳኝ የሆነውን ተልዕኮ መፈጸም እንደሚያስችል በአጽንዖት ገልጸዋል፡፡ ይህም የሥልጠናና የውይይት መድረክ በሁሉም መስክ የማስፈጸም አቅማችንን የሚያጎለብት ሲሆን በተቋማዊ ለውጥ ትግበራ፣ በመልካም አስተዳደር ማስፈንና

በሰው ሀብት አስተዳደር ዙሪያ ያሉ ብዥታዎችን ለመቅረፍ የሚረዳን ስለሆነ በጋራ መድረኩ ውይይት ላይ ሁሉም ሠልጣኝ የነቃ ተሳትፎ እንድታደርጉ አሳስባለሁ ብለዋል።

በዕለቱ መርሐ-ግብር መሠረት በመጀመሪያው ቀን ቅድሚያ የቀረበው የስብሰባ አመራር መመሪያ ሲሆን፣ አቅራቢውም አቶ ኢያሱ ገብሩ የውኃ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው፡፡ በይዘቱም፡- የስብሰባ አፈጻጸም አቅጣጫዎች፣ መሠረታዊ የስብሰባ ሕጎች፣ ውጤታማና ቀልጣፋ የስብሰባ አካሄድ፣ የሰብሳቢ፣ የተሳታፊዎች፣ የጸሐፊና የሰዓት-ተቆጣጣሪ ሚና፣ የቃለ ጉባኤ አያያዝ፣ የውሳኔ አሰጣጥ... የሚሉትን ያካተተ ነው፣

በመቀጠልም የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የሥነ-ምግባር ኮድ በአቶ ኢያሱ ቀርቦ ውይይት ተካሂዷል፡፡ አስራ ሁለቱ የሥነ-ምግባር መርሐዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ ሰነዱ አያይዞም ከቅርብ ኃላፊ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት፣ ከሥራ ባልደረቦች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት፣ በተጨማሪም ከኩባንያዎች፣ ከመገናኛ ብዙኃንና ከዓለም አቀፍ አካላት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ገለጻ ተደርጓል፡፡ ከገለጻዎቹም በኋላ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበው ምላሽ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ለሁለተኛው ቀን በተያዘው መርሐ ግብር መሠረት የውጤት ተኮር ሥርዓት /Balanced Score Card) የተሻሻለ ሰነድና የትግበራ ደረጃዎች አፈጻጸም ማኑዋል በወ/ሮ መሪማ የሱፍ የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ቀርቦ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲውን የቢኤስሲ ሁኔታ አቅርበዋል፡፡ ሰነዶቹ ረዘም ያሉና ጥልቅ ውይይት የተካሄደባቸው ሲሆን በተለይ በአፈጻጸም ላይ የተፈጠሩት ችግሮች በዝርዝር መዳሰሳቸው ታውቋል፡፡

በመርሐ-ግብሩ መሠረትም በቀጣዮቹ ቀናት የመልካም አስተዳር የሥልጠና ሰነድ እና የአተገባር ማኑዋል እና የዜጎች ቻርተር በአቶ ኢያሱ፣ የዜጎች ቻርተር ዝግጅትና የትግበራ ማኑዋል ይዘትና ማብራሪያ፣ የለውጥ መሣርያዎች ትስስር እንዲሁም የሕዝብ ክንፍ ተሳትፎና አቅም ግንባታ የአሠራር ማኑዋል በወ/ሮ መሪማ የሱፍ፣ የለውጥ ሠራዊት ግንባታ የመንግሥት ክንፍ ላይ ከውኃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በተጋበዙት በወ/ሪት ኮከቤ ፈለቀ ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

ይህ ሥልጠና በዋና መሥሪያ-ቤትም ሆነ በክልል አገልግሎት ማዕከላት በሁለት ዙር ተከፍሎ እንደሚሰጥና ከክልል አገልግሎት ማዕከላት የመጡ አመራሮችና ፈጻሚዎች የወሰዱትን የአሠልጣኞች ሥልጠና መሠረት በማድረግ በየማዕከላቸው ለሁሉም ፈጻሚ በሁለት ዙር ሥልጠና እንዲሰጡ በበላይ አመራ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

በዚሁ የአምስት ቀናት ሥልጠናዊ ውይይት ማጠቃለያ ላይ እንደተገለጸው እጅግ ጠቃሚ ግንዛቤና ክህሎት መቅሰማቸውን ተሳታፊዎቹ የገለጹ ሲሆን ተጋባዥ አሠልጣኞቹም በኤጀንሲው ሠራተኞች የነቃ ተሳትፎ እጅግ መደነቃቸውን ገልጸዋል፡፡ ቀጣዩ ርምጃ ሥልጠናውን ወደ ተግባር መቀየር እንደሆነ አጽንዖት ተሰጥቶታል፡፡



## ክላይሜት መረጃና መሣርያዎችን በመጠቀም የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ትንታኔ መስጠትና መተግበር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥልጠና ወርክ-ሾፕ ተካሄደ

የድርቅ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥርዓት መረጃ መረብን (FEWS-NET–Famine Early Warning Systems Network) የክላይሜት መረጃና መሣርያዎችን በመጠቀም የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ትንታኔ መስጠትና መተግበር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥልጠና ወርክ-ሾፕ ለሁለት ሳምንታት ቦሌ በሚገኘው የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት ተካሄደ

ሥልጠናውን የተካፈሉት ከአስራ አንዱም የክልል ሚቲዎሮሎጂካል ማዕከላት የተውጣጡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎችና ከማዕከል ደግሞ ከትንበያ፣ ከግብርና ሚቲዎሮሎጂ እንዲሁም ከመረጃና ክላይማቶሎጂ የተውጣጡ ባለሞያዎች መሆናቸው ታውቋል፡፡ የሁለቱን ሳምንት ሥልጠና የሰጡት ዶ/ር ድሪባ ቆርቻ እና ሚስተር ዲጎ ፔድሪሮስ ከዩስ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ማዕከል FEWS-NET መሆናቸው ታውቋል፡፡


የሥልጠናው አስተባባሪ አቶ አመኑ ሂርኮ እንደገለጹት በዐውደ-ጥናቱ ላይ ተገኝተው ሥልጠናውን የሰጡት በሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ መስክ ከፍ ያለ እውቀት ያላቸው ምሑራን መሆናቸውን አስታውቀው ሠልጣኞቹም በተለይ ዘመናዊውን የትንበያ ሞዴሎችና ማሳያዎች በሚገባ ለመጠቀም አቅማቸውን እንደሚያዳብር ገልጸዋል፡፡

FEWS-NET በተለይ እንደ ድርቅ ያሉ ጎጂ የአየር ሁኔታ ክስተቶችን ለመቋቋም ቅድመ-ማስጠንቀቂያዎችን ለማድረግ

የሚያስችሉ ሶፍትዌሮችን በማውጣት ለግብርና ሚቲዎሮሎጂ ትንታኔ በማድረግ ላይ መሆኑንና የዚህ ሥልጠና ዋነኛ ዓላማም የባለሙያዎችን ክህሎት በማዳበር በዘርፉ የተሻለ እገዛ እንያደርጉ ማስቻል መሆኑም ተገልጿል፡፡

በሥልጠናው መጨረሻ ላይ ያገኙትን እውቀት ተግባራዊ በማድረግ በስድስት ቡድኖች በመመደብ ያዘጋጁትን በሶፍትዌር ውጤት መጠቀም የጥናት ጽሑፍ የበላይ አመራሮቹ ባሉበት ማቅረባቸው ታውቋል፡፡

በሁለት ሳምንቱ ሥልጠና ማጠቃለያ ላይ ለሠልጣኞቹ የምስክር ወረቀት የሰጡት የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ሲሆኑ ሥልጠናው የተሳካ እንዲሆን የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ያደረጉትን በተለይም የሥልጠናውን ወጪ የሸፈኑትን FEWS-NET፣ USAID, USGS የተባሉትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አመስግነዋል፡፡ በመዝጊያው ሥነ-ሥርዓት ላይ በኢትዮጵያ የ FEWS-NET ተወካይ ተገኝተው መልዕክት ማስተላለፋቸው ታውቋል፡፡



የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ ምሑራኑ ሥልጠናውን ሲሰጡ

## አስራ ሁለተኛው የነጭ ሪቫን ቀን በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በደማቅ ሁኔታ ተከበረ

በዓሉ የተከበረው ዓርብ ህዳር 22 ቀን 2010 ዓ.ም **"በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመከላከልና ለማስወገድ የወንዶች አጋርነትን እናረጋግጥ** !""STRENGTH MALE ENGAGEMENT FOR PREVENTION AND ELIMINATION OF VIOLENCE AGAINST WOMEN & GIRL" **በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፍ ለ 26ኛ ጊዜ በአገር አቀፍ ለ12ኛ ጊዜ** ቦሌ በሚገኘው የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሁሉም ሠራተኞች በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተከበረ፡፡

በመክፈቻ ንግግር ላይ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አማካሪ የሆኑት አቶ ታፈሰ ረጋሳ በሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በተዘጋጀው የነጭ ሪቫን በዓል ቀን ንግግር እንዳደርግ በመጋበዜ የተሰማኝን ደስታ እየገለጽኩ ቀኑን ለማክበር የተገኛችሁት ሁሉ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት፤ በዓሉን ስናከብር ማስታወስ የሚገባን ሴት እናት፣ ሴት እህት ፣ ሴት ሚስት ፣ ሴት ልጅ መሆኗንና ይህንን እንደ አገራዊ ባህል በመያዝ በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን ማንኛውንም ዓይነት ጎጂ ባህላዊ ጥቃቶችን በመዋጋት አጋርነታችን እናረጋግጥ በማለት ገልጸዋል፡፡

በመቀጠልም የኤጀንሲው የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ አልማዝ ታደሰ በዓሉን አስመልክቶ ባቀረቡት ጹሁፍ የነጭ ሪቫን ቀን ታሪካዊ አመጣጥ ሲገልጹ ከኖቬምበር 29 እስከ ዲሴምበር 6 ባሉት ተከታታይ 16 ቀናት እንዲከበር መነሻ የሆነው በካናዳ ሞንትሪ ኢንጂነሪንግ ትምህርት ቤት ውስጥ አክራሪ የሴት

እንቅስቃሴ መሪዎች በሚል በአንድ ወንድ የተገደሉትን 14 ሴቶችና ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚሞቱትን ለማስታወስ ነው፡፡ ወደ አገራችንም ስንመጣ ነጭ ሪባን ወንዶች የደረት ኪስ በማድረግ በሴቶች ላይ ማንኛውም ዓይነት ጥቃት ላለመፈጸም እና ጥቃቱ በሌሎች ሲፈጸም ዝም ላለማለት የሚገቡት ቃል ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

ጾታዊ ጥቃት ስንል ሆን ተብሎ ለመጉዳት የሚደረግ በተለያዩ ቦታዎች ሊፈጸም የሚችል ሲሆን ፤ በማንና የት ይፈጸማል በቤተሰብ ፣በጓደኛ፣ በጎረቤት፣ እና በስራ አጋር በማንኛውም ቦታ ወይም በአንድ ቤት ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች መካከል ሊፈፀም የሚችል መሆኑ፣ ጥቃቱም በአካል ላይ ብቻ ሳይሆን በስነ ልቦና ላይም ጉዳት የሚያስከትል እና ጥቃቱ ከስነ ልቦናዊ ጉዳት አንጻር ሲታይ የአንድን ሰው ክብር በስድብ፤ በማንቋሸሽ፤ በማዋረድ፤ ባለማናገር፤ ቃልን ባለማክበር፤ በማስፈራራት፤ በተጠቂ ወይም በተጠቂ የቅርብ ሰዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ በመዛትና በመሳሰሉት ምክንያቶች የሚፈጸም መሆኑን በሰፊው አብራርተዋል፡፡ በሌላ መልኩ የሴቶች ጥቃት የማህበረሰብ ስህተት ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበትና ሴቶችም መብታቸውን በማወቅ የመጠየቅና በተሰጣቸውን እድል የመጠቀም አቅማቸውን ማጎልበት፣ ሴቶችን ማብቃት፣ ወደ ውሳኔ ሰጭነት እንዲደርሱ መስራት፣ በሴቶች ላይ ጥቃት እንዳይፈጸም ህብረተሰቡን ማዕከል ያደረገና ያሳተፈ የመከላከል ስራ መሰራት እንዳለበት በሰፊው ገልጸዋል፡፡

በአንድ ቀን ክብረ በዓል የሴቶችን ጥቃት ማውራት መፍትሄ እንደማይሆን በመግለጽ በመንግስት በኩል በጥንቃቄ መሰራት እንዳለበት ከተሳታፊዎቹ ተነስቷል፡፡ በመቀጠል ይህ የነጭ ሪቫን ቀን ጥቃት የሚደርስባቸውን ሴቶች ከህብረተሰቡ ጎን መቆም ወንዶችም

ሀላፊነት ያለባቸው መሆኑን ለአቶ አሰፋ የመስሪያ ቤቱን ወንዶች በመወከል የቃል ኪዳን ሪቫን አበርክተውላቸዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ሰለሞን ለማ የኤጀንሲው የህግ ባለሙያ የቤተሰብ ህግ ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ አሁን ከተሻሻለው ህግ ጋር ያለው ልዩነት ምን ይመስላል በሚል አጠር ያለ ጹሁፍ በማቅረብ እና በቀረበው ጽሑፍ ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ የፕሮግራሙ ፍጻሜ ሆኗል፡፡




12ኛው የነጭ ሪባን ቀን በድምቀት ሲከበር